የወ/መ/ቁጥር 159854

የልደታ ምድብ 5 ኛ ወንጀል ችሎት

ሐምሌ 14 ቀን 2002 ዓ.ም ከቀኑ 8፡00 ሰዓት

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፡ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፡ 1 ኛ አቶ እስክንድር ከበደ አበበ - ቀረቡ

2 ኛ አቶ ካሳሁን ከበደ ኃይሉ - ቀረቡ

3 ኛ ወ/ሪት ሕይወት ግርማ አዲስ - ቀረበች

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ፡፡

<u>ፍርድ</u>

ዐ/ሕግ ጥር 13 ቀን 2002 ዓ.ም በተባ፟ፈ የወንጀል ክስ አቤቱታ በአንደኛው ክስ አንደኛ ተከሳሽ በ 1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 703(1) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ ተከሳሽ በሕግ ወይም በውል ግዴታ ንብረት አንዲያስተዳድር በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ተሰጥቶት እያለ ሚያዝያ 21 ቀን 2001 ዓ.ም በግምት ከረፋዱ 4፡00 ሰዓት ሲሆን በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/05 ክልል ልዩ ቦታው ዘነበወርቅ ታቦት ማደሪያ አካባቢ በሚገኘው የኢትዮጵያ አሶሴሽን ፎር ሂውማን ራይትስ ዋና መ/ቤት ውስጥ መጋቢት 29 ቀን 2001 ዓ.ም በተደረገ የቦርድ አባላት ስብሰባ ላይ የቦርድ አባል ያልሆኑ አቶ ግርማይ ከበደ እና አቶ አመሀ በድሉን የቦርድ አባል በማስመሰልና ውሳኔ በማሰጠት በሚያዝያ 21 ቀን 2001 ዓ.ም በቼክ የመፈረም ስልጣን በሌላቸው ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሳሾችን በማስፈረም 22,150.00(ሃያ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሃምሳ ብር) የማህበሩን ገንዘብ በወ/ሮ መሰሉ መስቀሌ ስም ወጪ እንዲሆን በማድረጉ በፈፀመው በሌላ ሰው የስራ አመራር ላይ የተፈፀመ ከባድ ጉዳት ማድረስ ወንጀል፤ በሁለተኛው ክስ ደግሞ አንደኛ ተከሳሽ በ 1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 446(ለ) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ ተከሳሹ የምርመራ ስራን ለማሳሳት በማሰብ ግንቦት 13 ቀን 2001 ዓ.ም ለኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ በቁጥር ኢሁር/በ 20/2009 በተባ፟ፈ ማስረጃ የኢትዮጵያ አሶሴሽን ፎር ሂውማን ራይትስ ውስጥ መስራች አባላት 5/አምስት/ ብቻ ሆነው እያለ 22/ሃያ ሁለት/ አባላት መስራች ናቸው በማለት የተሳሳተ መረጃ የሰጠ በመሆኑ በፈፀመው የፍትህን ስራ ማሳሳት ወንጀል ተከሷል በማለት ያቀረበ ሲሆን፤ በሦስተኛው ክስ ደግሞ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሳሾች በ 1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1)(ሀ) እና 382(1) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ የሌላ ሰውን ጥቅም ለመጉዳት በማሰብ በኢትዮጵያ አሶሴሽን ፎር ሂውማን ራይትስ ስም በተዘጋጀ ቼክ ላይ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሳሾች ለመፈረም ስልጣን ሳይኖራቸው ሦስተኛ ተከሳሽ የማህበሩ አባል ጭምር ሳትሆን ሚያዝያ 21 ቀን 2001 ዓ.ም ከዳሸን አብይ ባንክ

ከተንቀሳቃሽ ሂሳብ ቁጥር 000151947014 ውስጥ ባዘጋጁት ሀሰተኛ ቼክ 22,150.00(ሃያ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሃምሳ ብር) አውጥተው ለግል ጥቅማቸው ያዋሉ በመሆኑ በፈፀሙት በዋና ወንጀል አድራጊነት የንግድ ወይም ተላላፊ የዋስትና ሰነዶችን ወደ ሐሰት መለወጥና ማጥፋት ወንጀል ተከሰዋል በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሾች ደርሷቸውና ተነቦላቸው ከተረዱት በኋላ ክሱን ሳይቃወሙ፤ ድርጊቱን አልፈፀምንም፤ ጥፋተኞችም አይደለንም ብለው ክደው በመከራከራቸው ዐ/ሕግ ማስረጃዎችን በማቅረብ አሰምቷል:: ይሄውም ሦስት የሰው ምስክሮችንና የሰነድ ማስረጃዎችን በማቅረብ ያሰማ ሲሆን ፍ/ቤቱም እነዚህን ማስረጃዎች በመመርመር መጋቢት 09 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ዐ/ሕግ እንደ ክስ አቀራረቡ ያስረዳ ስለሆነ ተከሳሾች በተከሰሱበት ድንጋጌዎች ስር እንዲከላከሉ በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት ታዘዋል።

አንደኛ፤ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሳሾችም እንከላከላለን ብለው የመከላከያ ምስክሮችንና የሰነድ ማስረጃዎችን በማቅረብ ያሰሙ ሲሆን አንደኛ ተከሳሽ ሦስት የመከላከያ ምስክሮች፤ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሳሾች ደግሞ በጋራ አንድ የመከላከያ ምስክር ያቀረቡ ሲሆን በመከላከያ ጭብጥነትም ያስመዘገቡትን ስናይ አንደኛ ተከሳሽ መጋቢት 20 ቀን 2001 ዓ.ም በተደረገ ጠቅላላ ጉባኤ ሁለት ሰዎች የቦርድ አባል ተደርገው መመረጣቸውን፤ እነዚህ አባላት የተመረጡበት ቃላ ጉባኤ በጠቅላላ ቃላ ጉባኤ ሐምሌ 05 ቀን 2001 ዓ.ም የፀደቀ መሆኑን ያስረዱልኛል በማለት ሲያስመዘግቡ፤ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሳሾች ደግሞ በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/05 የቤት ቁጥር አ.33 የማህበሩ ገንዘብ ያዥ ሆነው ሲሰሩ በሚያዝያ 21 ቀን 2001 ዓ.ም ወጪ የተደረገውን ገንዘብ በማህበሩ ህጋዊ ቼክ ወጪ ማድረጋቸውን እና ለተፈለገው ዓላማ የዋለ መሆኑን እናስረዳለን የሚለውን ሲሆን በዚሁ መሰረት የመከላከያ ምስክሮቹ ቀርበው መታላ ፈፅመው የመሰከሩ ሲሆን ቃላቸውም ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ይገኛል።

ተከሳሾች ባቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበባቸውን ክስና ማስረጃ አስተባብለዋል ወይ የሚለውን ነጥብ የመረመረ ሲሆን አንደኛ ተከሳሽ የኢትዮጵያ አሶሴሽን ፎር ሂማንን ራይትስ ማህበር የጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ እንዲሁም የዚሁ ማህበር ቦርድ ሰብሳቢ መሆኑ ከቀረቡት የሰነድና የሰው ማስረጃዎች የተረጋገጠና ተከሳሹም ያልካደው ጉዳይ ነው። ይህ በእንዲህ እያለ መጋቢት 20 ቀን 2001 ማህበሩ ጠቅላላ ጉበኤ ጠርቷል ተብሎ በዚሁ ስብሳባ ከአባለቱ ውስጥ ከግማሽ በላይ ስለተገኙ ስብሰባው ቀጥሎ ጉባኤው ውሳኔዎችን አሳልፏል፤ ከእነዚህ ውስጥም አቶ አመሀ በድሉንና አቶ ግርማይ ከበደን በቦርድ አባልነት የመምረጡ ሂደት ነው። እነዚህን የተመረጡትን የቦርድ አባላት የያዘው ቦርድ መጋቢት 29 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰብስቦ ውሳኔዎችን አሳልፏል፤ በዚህም መሰረት ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሳሾችን የማህበሩ ቼክ ፊራሚዎች ተደርገው ተሹመዋል። ይህ ማለት ደግሞ ቀድሞ የማህበሩን ቼክ ይፈርሙ የነበሩትን ግለሰብ የመለወጥ ሁኔታ ነው።

አንደኛ ተከሳሽ በሕግ ወይም በውል ግዴታ የማህበሩን የንብረት ጥቅም እንዲጠብቅ ወይም ሥራውን እንዲመራ ተደርጎ እያለ ወይም በተሰጠው ኃላፊነት ያለአግባብ በመገልገል ወይም የተጣለበትን ግዴታ ባለመፈፀም በሚጠብቀው የንብረት ጥቅም ላይ ወይም ለሚሰራበት ማህበር በሚፈፅመው አገልግሎት ላይ አስቦ ጉዳት አድርሷል ተብሎ ክስ የቀረበበት ሲሆን ዐ/ሕግ የአንደኛ ተከሳሽን ኃላፊነት በሕጉ ላይ ከተመለከተው አንፃር ያስረዳ ቢሆንም

በተከሳሹ ሥራውን ወይም የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ባለመገልገሉ በማህበሩ ላይ የደረሰውን ጉዳት እንዲያስረዳ ሲጠየቅ፤ መጋቢት 29 ቀን 2001 ዓ.ም ቦርዱ በወሰነው መሰረት ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሳሾች ቼክ እንዲፈርሙ በሰጣቸው ስልጣን መሰረት እነዚሁ ሁለት ተከሳሾች ብር 22,150.00(ሃያ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሃምሳ ብር) የያዘ ቼክ በመፈረማቸው ገንዘቡ ወጪ የተደረገ ስለሆነ፤ ይህ ደግሞ ጉዳት ነው፤ ምክንያቱም ሕጋዊ ስልጣን በሌለው ቦርድ ለፈራሚዎቹ በተሰጠ ስልጣን ቼኩ ተፈርሞ ገንዘቡ የወጣ ስለሆነ ይህ ጉዳት ነው በማለት አስረድቷል። መጋቢት 20 ቀን 2001 ዓ.ም የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የተደረገ ስለመሆኑ በተከሳሾች በኩል የቀረቡት የመከላከያ ምስክሮች ሲያስረዱ፤ በዕለቱ ቃለ ጉባኤ እንዲፃፍ የተደረጉት ወ/ሮ ፀሐይ የተባሉት የጠቅላላ ጉበኤው ፀሐፊ ናቸው በማለት ገልፀዋል። በዚህ ጠቅላላ ጉባኤ አቶ አመሀ በድሉና አቶ ግርማይ ከበደ የተባሉት የማህበሩ አባላት የቦርድ አባላት ሆነው የተመረጡ መሆናቸውን አስረድተዋል። እነዚህ የተመረጡ የቦርድ አባላት ያሉበት ቦርድ ደግሞ መጋቢት 29 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰብስቦ ውሳኔዎችን ያሳለፈ ስለመሆኑ የቀረበው የዕለቱ የቦርዱ ቃለ ጉባኤ ያስረዳል። ይህ ቦርድ በሰጠው ውሳኔ ደግሞ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሳሾችን የማህበሩ የቼክ ፈራሚዎች አድርጎ የሾማቸው መሆኑን የቦርዱ ውሳኔ ያስረዳል። እነዚህ በቦርዱ የቼክ ፈራሚ ሆነው የተሾሙ ሰዎች ደግሞ ብር 22,150.00(ሃያ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሀምሳ ብር) የያዘ ቼክ ፈርመው ወ/ሮ መሰሉ መስቀሌ የተባሉ የማህበሩ ገንዘብ ያዥ ወጪ አድርገውት ገንዘቡም ለማህበሩ የቤት ኪራይ ዕዳ ክፍያ፤ ለሰራተኞች ደመወዝ ክፍያ፤ ለስልክና ሌሎች የማህበሩ ልዩ ልዩ ወጪዎች የዋለ ስለመሆኑ ወ/ሮ መሰሉ መስቀሌ ቀርበው በምስክርነት ያስረዱ ሲሆን፤ የሰነድ ማስረጃም ቀርቧል። ይህ ክፍያ መጋቢት 29 ቀን 2001 ዓ.ም የተሰበሰበው ቦርድ ተሰብስቦ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሳሾችን የማህበሩን ቼክ ፈራሚ ባያደርግም ሊከፈል የሚገባው ዕዳ ስለመሆኑ የቀረቡት የክፍያ ማስረጃዎች የሚያረጋግጡት ነው። በመሆኑም ብር 22,150.00(ሃያ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሃምሳ ብር) የያዘ ቼክ በሁለቱም ተከሳሾች ተፈርሞ በወ/ሮ መሰሉ መስቀሌ አማካኝነት ወጪ መሆኑና ለማህበሩ አገልግሎት መዋሉ አንደኛ ተከሳሽ በማህበሩ ላይ አስበው ጉዳት አድርሰዋል የሚያስብል ድርጊት ሆኖ ፍ/ቤቱ አላገኘውም። ይህ ማለት ግን መጋቢት 20 ቀን 2001 ዓ.ም የማህበሩ ጠቅላላ ጉበኤ ተደርጎ የተወሰነው ውሳኔ እና በኋላም ሐምሌ 05 ቀን 2001 ዓ.ም በአስቸኳይ ስብሰባ የፀደቀው የመጋቢት 20 ቀን 2001 ዓ.ም ቃለ ጉባኤ የማህበሩን ሕግና ደንብ ተከትሎ የተሰጠ ውሳኔ ነው ማለት አይደለም። ምክንያቱም የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ሕግን፤ ደንብንና ሥርዓትን አልተከተለም ከተባለ በፍትሐብሔር ሕግ አንቀፅ 448 እና በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ቁጥር 309(1) መሰረት ቅሬታ ባለው አካል አማካኝነት አቤቱታ ሲቀርብበት የሚታይ በመሆኑ ነው። በመሆኑም አንደኛ ተከሳሽ በአንደኛው ክስ በማህበሩ ላይ ከባድ ጉዳት አድርሷል ተብሎ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 703(1) ተጠቅሶ የቀረበበትን የወንጀል ክስ ባቀረበው የመከላከያ ማስረጃ በማህበሩ ላይ ከባድ ጉዳት ያለማድረሱን ያስተባበለ ስለሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(2) መሰረት በነፃ ተሰናብቷል።

በሦስተኛው ክስ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሳሾች የወንጀል ሕግ አንቀፅ 382(1) ላይ የተደነገገውን ተላልፈው የማህበሩን ቼክ ለመፈረም ስልጣን ሳይኖራቸው በመፈረም ብር 22,150.00(ሃያ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሃምሳ ብር) ወጪ በማድረግ ለግል ጥቅማቸው አውለዋል በማለት የቀረበባቸውን ክስ በተመለከተ በመጀመሪያ

ደረጃ ሁለቱም ተከሳሾች ፊርማቸውን ያስቀመጡበት ቼክ የማህበሩ ንብረት የሆነ ቼክና በወ/ሮ መሰሉ መስቀሌ እጅ የነበረ ሲሆን፤ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሳሾች የማህበሩ ቦርድ መጋቢት 29 ቀን 2001 ዓ.ም ባደረገው ስብሳባ እነዚህ ሁለት ተከሳሾች የማህበሩን ቼክ ፈራሚ እንዲሆኑ ተወስኖ፤ ይሄው ውሳኔም በቦርዱ ስብሳቢ የደረሳቸው ሲሆን፤ ቼኩንም የፈረሙት ከቦርዱ በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት በመሆኑ፤ ስልጣን ሳይኖራቸው ፈርመዋል ሊባሉ አይችልም። ከዚህ ሌላ ቼኩን እነዚህ ሁለት ተከሳሾች ከፈረሙበት በኋላ ቼኩን በመያዝ ወደ ባንክ በመሄድ የመነዘሩት የማህበሩ ሰራተኛ የሆኑት ወ/ሮ መሰሉ መስቀሌ ሲሆኑ፤ ይህ ገንዘብም ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ወጪ ተደርጎ ለግለሰቦች በተለይም ለሁለተኛ እና ሦስተኛ ተከሳሾች ጥቅም የዋለ ሳይሆን ለማህበሩ ጥቅም ስለመሆኑ የሰነድና የሰው የመከላከያ ማስረጃ ተከሳሾች አቅርበው ያስረዱ ስለሆነ፤ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 382(1) ተጠቅሶ የቀረበባቸውን ክስና ማስረጃ ባቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ ያስተባበሉት ስለሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(2) መሰረት በነፃ ተሰናብተዋል።

ሁለተኛውን ክስ በተመለከተ አንደኛ ተከሳሽ በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ በኩል ግንቦት 05 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የተጠየቀው መረጃ 1ኛ) አቶ አበባው አስፋው እና አቶ ሻፊር መሀመድ የመ/ቤቱ ሰራተኛ መሆን ያለመሆናቸው እና ኃላፊነታቸው፤ 2ኛ) የመ/ቤቱ ሰራተኛ ከሆኑ እስከ መቼ ድረስ በስራ ላይ እንዳሉ፤ 3ኛ) የታገዱም ከሆነ ከመቼ ጀምሮ እንደታገዱ እና የእግድ ደብዳቤ እንደረሳቸው እና እንዳልደረሳቸው፤ 4ኛ) በኃላፊነት ላይ ከነበሩ እነሱም ከኃላፊነታቸው ቦታ ለማንሳት እና ሌሎችን ለመተካት ምን ያህል የቦርዱ አመራሮች ወይም አባላት ተገኝተው ማንሳት እንደሚችሉ እና የመ/ቤቱ የመተዳደሪያ ደንብ ካለ በማጣቀስ እንዲላክልን፤ 5ኛ) እንዲሁም ግለሰቦቹ በሌሉበት ቦታ ገንዘብ ከባንክ ማውጣት የሚቻል መሆን ያለመሆኑን አብራርታችሁ እንድትገልፁልን የሚል ሲሆን ይህን መሰረት በማድረግ አንደኛ ተከሳሽ ግንቦት 13 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በሰጡት መልስ ላይ ዝርዝር ጉዳዮችን በሰፊው የገለፁ ሲሆን፤ በዚህ ውስጥም የኢትዮጵያ አሶሴሽን ፎር ሂውማን ራይትስ በ22 መስራች አባላት የተቋቋመ ሕጋዊ ማህበር ነው የሚል መልስ ጭምርም ሰጥቷል። የክፍሉ ፖሊስ መረጃውን የጠየቀው ምርመራውን ለማከናወን ሲሆን፤ አንደኛ ተከሳሽ ግን የማህበሩ መስራች አባል አንዱ ራሱ መሆኑን እያወቀና የመስራች አባለት ቁጥርም 5 ሆነው እያለ 22 ናቸው ብሎ መግለፁ የፍትህን ሥራ ማሳሳት ወንጀል ስለሆነና ባቀረበው የመከላከያ ማስረጃ ለማስተባበል ያልቻለ በመሆኑ አንደኛ ተከሳሽ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 446(ለ) ስር ጥፋተኛ ነው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>የቅጣት አስተያየት</u>

<u>ዐ/ሕግ</u>፡ የቅጣት ማክበጃም ሆነ ማቅለያ የለንም፤ ነገር ግን የወንጀል ደረጃው ከባድ

ይባል ምክንያቱም ድርጊቱ ማህበሩ የተቋቋመበትን ዓላማ የሚያሳስትና

የድርጊቱም አፈፃፀም ሲታይ ያልተጠየቀን መረጃ በመስጠት ለማሳሳት

የሞከረ ስለሆነ ነው በማለት አመለከቱ

<u>አንደኛ ተከሳሽ</u>፡ ዕድሜዬ 37 ዓመት ነው፤ ትዳር አለኝ፤ ልጅ አንድ የ6 ዓመት

አለኝ፤ የትምህርት ደረጃ የመጀመሪያ ዲግሪ በውጭ ቋንቋና ሥነ ፅሑፍ አለኝ፤ አሁን የምሰራው በኢፌዴሪ ሕዝብ እንባ ጠበቂ ውስጥ ነው፤ የወር ገቢ ብር 2,700.00(ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ብር) ነው፤ ባለቤቴ ሥራ የላትም፤

ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ቅጣት ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ሊሆን እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወሰነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትህዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ክብደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

አንደኛ ተከሳሽ አሁን ጥፋተኛ የተባሉበት በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 446(ለ) /የፍትህን ሥራ ማሳሳት ወንጀል ገና ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ የወንጀል ደረጃ እና እርከን የሚወሰነው በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 13 መሰረት ነው። የደረጃ አወሳሰኑም ማክበጃውና ማቅለያው ታሳቢ ከመደረጉ በፊት በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት እንደሚወሰን መመሪያው በደነገገው መሰረት ደረጃው በሦስት ደረጃዎች ሀ. ዝቅተኛ፤ ለ. መካከለኛ እና ሐ. ከባድ ደረጃ በማለት ይለያል።

ፍ/ቤቱም በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት ወንጀሉ የተፈፀመው አንደኛ ተከሳሽ የሰዎችን ሰብአዊ መብት ለማስከበር የተቋቋመ ግብረሰናይ ድርጅት ኃላፊ ሆነው፤ በዚሁ ድርጅት አሰራር በተመለከተ የወንጀል አቤቱታ ቀርቦ ይህንኑ ፖሊስ ለማጣራት በሚያደርገው ሂደት መረጃ ሲጠየቁ ትክክለኛ መረጃ ያውም ባለተጠየቁበት ነጥብ ላይ የሰጡ በመሆኑ የወንጀል ደረጃው ከባድ ነው ተብሎ ተወስኗል።

በወጣው ደረጃ መሰረት ቅጣቱን ለመወሰን በሕጉ አንቀፅ 446(ለ) ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ያስቀጣል ተብሎ የተደነገገ ስለሆነ ከሁለቱ የቅጣት አይነቶች

ፍ/ቤቱ በቅድሚያ አንዱን መምረጥ ስላለበት ተከሳሽ አንድ አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ አባት እና የቤተሰቡ የገቢ ምንጭ በመሆናቸውና ይህ የተከሳሹ የመጀመሪያ ጥፋት ስለሆነ በእስራት ከመቅጣት በገንዘብ መቀጮ መቅጣት አግባብ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ተከሳሽ በገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል።

ፍ/ቤቱ ተከሳሽን በገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ከወሰነ ደግሞ በመመሪያው አንቀፅ 13(10) መሰረት የሚወሰን ሲሆን፤ በዚህም መሰረት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 446(ለ) የገንዘብ መቀጮው ከብር አስር እስከ አንድ ሺህ ብር ስለሆነና የወንጀል ደረጃው ከባድ በመሆኑ መነሻ ቅጣቱ የጣሪያው ብር አንድ ሺህ ሁለት ሦስተኛ ተቀንሶ በሚገኘው ውጤት እና በጣሪያው ብር አንድ ሺህ መካከል ይወሰናል። የብር አንድ ሺህ ሁለት ሦስተኛ ውጤት ብር ስድስት መቶ ስልሳ ሰባት ብር ስለሚሆን ቅጣቱ በብር ስድስት መቶ ስልሳ ሰባት እና በብር አንድ ሺህ ብር መካከል ይወሰናል። ፍ/ቤቱም የተከሳሽ የወር ገቢን መሰረት በማድረግና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸውን ከግንዛቤ በማስገባት ቅጣቱ ብር 800.00(ስምንት መቶ ብር) መነሻ ቅጣት እንዲሆን ተወስኗል። ይህን መነሻ ቅጣት ይዘን ወደ መመሪያው አባሪ ሁለት ስንሄድ ይህ የብር 800.00(ስምንት መቶ ብር) የገንዘብ መቀጮ በአባሪ 2 እርከን 1 ስር የሚወድቅ በመሆኑ፤ የእርከን 1 ፈቃደ ስልጣን ደግሞ እስከ ብር አንድ ሺህ ድረስ ስለሆነ ፍ/ቤቱ በዚሁ ፍቅድ ስልጣን መሰረት አንደኛ ተከሳሽ በብር 1000.00(አንድ ሺህ ብር) እንዲቀጡ ተወስኗል።

በወ/ሕግ በኩል የቅጣት ማክበጃ ተጠይቆ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84 መሰረት የቀረበ ነገር ባለመኖሩ ከላይ የተወሰነው ቅጣት የሚከብድበት ምክንያት የለም። በተከሳሽም በኩል በማስረጃ የተደገፈ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ስላልቀረበ ፍ/ቤቱ ከላይ የወሰነውን መጠን ብር 1000.00(አንድ ሺህ ብር) ን ተከሳሽ በመቀጮነት እንዲከፍሉ ወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. አንደኛ ተከሳሽ የቅጣት ገንዘቡን ሲከፍሉ ለማ/ቤት መፍቻ ይግፉ።

2 ኛ. በዚህ መዝገብ የተገባ የዋስትና ግዴታ ቀሪ ሆኗል።

3 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

4 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።